# በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት

# ከተቋቋመበት (1968 ዓ.ም) ጀምሮ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና የተገኙ ዉጤቶች

“Facts about Ethiopia” በሚል ለሚታተም ሀገራዊ የመረጃ መፅሃፍ የቀረበ

**ፖ.ሣ.ቁ. 30726**

**ሥ.ቁ. 0116612244**

**0116627396**

**ኢሜይል፡** info@ibc-et.org

**አዲስ አበባ**

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ባላት የተለያየ መልክዓ ምድር አቀማመጥና የአየር ንብረት ምክንያት ሰፊና ከፍተኛ ተለያይነት ያለው የብዝሀ ሕይወት ስብጥር የሚገኝባትና በዓለም በዚህ ፀጋ በከፍተኛ ደረጃ ከሚታወቁት ጥቂት አገሮች ውስጥ አንዷ ናት፡፡ ይህ በዕፅዋት፣ በእንስሳትና በደቂቅ ዘአካላት የሚካተተው የብዝሀ ሕይወት ሀብት ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለጤና ዘርፎችና ለሌሎች የልማት ተግባራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማበርከቱም በላይ ለህልውናቸውና ቀጣይነታቸው መሠረት ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ መከሰት፣ የድርቅና ምድረ በዳነት መስፋፋት፣ በተለይ በታዳጊ አገሮች የሕዝብ ቁጥር ከልማት ዕድገት ጋር ባልተመጣጠነ ሁኔታ መጨመር እንዲሁም የብዝሀ ሕይወት ጥበቃን ያላገናዘቡ ልማቶችና ሀብቱን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠቀም ካለመቻል የተነሣ ይህ ሀብት መልሶ ሊተካ በማይችልበት ሁኔታ እየተመናመነ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ የሚገኘውን የብዝሀ ሕይወት ሀብት በሚገባ የመቃኘት፣ የመሰብሰብ፣ ጠብቆ በዘላቂነት የማቆየትና ተመራምሮ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ ቅድሚያ ትኩረት መሠጠት እንዳለበት ግንዛቤ እየሰፋ መጣ፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያዊያንና ዓለምአቀፍ ሳይንቲስቶች በየጊዜው ባደረጉት ግፊት የዓለማቀፉ የግብርና ምርምር አማካሪ አካል (Consultative Group for International Agricultural Research) በ1968 ዓለምአቀፋዊ ቅንጅት ያላቸው የዕፅዋት ጀኔቲክ ሀብት ማዕከሎች (ጅን ባንኮች) እንዲቋቋሙ በወሰነው መሠረት ሀገራችን ካላት ሰፊ የጀኔቲክ ሀብት አንጻር ማዕከሉ እንዲቋቋም እድል ከተሰጣቸው ሀገሮች አንዷ ሆና ተመረጠች፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት ከጀርመን ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በተደረገለት እገዛ በ1968 ዓ.ም. ይህ ተቋም የዕፅዋት ጄኔቲክ ሀብት ማዕከል በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡ በመቀጠልም መንግሥት የተቋሙን ሀላፊነት በማስፋትና አቅሙን በማሳደግ በኢንስቲትዩት ደረጃ እንዲደራጅ ተደረገ፡፡

ስለሆነም ኢንስቲትዩቱ ሀገሪቱ ያላትን የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የደቂቅ ዘአካላት የብዝሀ ሕይወት ሀብትና እነዚህን አቅፎ የያዘውን ሥርዓተ-ምህዳር (Ecosystem) የመጠበቅ የማልማትና በዘላቂነት ጥቅም ላይ የማዋልን ሥራ የመምራት፣ የማስተባበርና የመከታተል ኃላፊነትን ለመወጣትና ከሀብቱ የሚገኘውን ጥቅም ለሀገሪቱና ለህብረተሰቡ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማስገኘት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

## 2. ዓላማ

የሀገሪቱ የብዝሀ ሕይወት ሀብት እንዲጠና፣ በአግባቡ እንዲጠበቅ፣ እንዲበለፀግና ለዘላቂ ጠቀሜታ እንዲውል በማስቻል ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ብልፅግናና ልማት ወሳኝ ሚና መጫወቱን ማረጋገጥ ነው።

## 3. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ተግባራት

- በሀገሪቱ ያለውን ሕይወታዊ ሀብት በሚገባ መቃኘት፣ መሰብሰብ፣ ጠብቆ በዘላቂነት ለማቆየትና ጥቅም ላይ ለማዋል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የብዝሀ ሕይወት ሀብት ጥበቃ መርሃ ግብሮች ከፌደራላዊና ከክልላዊ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የጤና እንዲሁም ሌሎች የልማት ስትራቴጅዎችና ዕቅዶች ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ፣
- ኢትዮጵያ አባል በመሆን የተቀበለቻቸው የሕይወታዊ ሀብት ጉዳይን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ውሎችና ግዴታዎችን በተግባር እንዲፈፅሙ መሥራት፣
- የሀገሪቱ ሕይወታዊ ሀብት መረጃዎች የሚጠበቁበትንና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሥርዓት መዘርጋት፣
- የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ወዘተ... ናቸው።

## 4. ኢንስቲትዩቱ የሚመራባቸው ስምምነቶች፣ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና፣ ስትራቴጂዎች

- ዓለም አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ስምምነት (1990)፣
- ብሄራዊ የብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ምርምር ፖሊሲ (1990)፣
- የብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ (ቁ. 120/1990)፣
- የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ማሻሻያ አዋጅ (ቁ. 381/1996 )፣
- የጄነቲክ ሀብትና የማኅበረሰብ እውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ (ቁ. 482/1998)፣
- ብሄራዊ የብዝሀ ሕይወት ስትራቴጂና አክሽን ፕላን (1997)፣
- የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የአምስት አመት መርሀ ግብር እቅድ፣

# 5. የኢንስቲትዩቱ አብይት ክንውኖች

## 5.1 የአዝርዕት ጀኔቲክ ሀብት

 

- 28 የአዝርዕት ዝርያዎችን ሚወክሉ ከ60 ሺህ በላይ ናሙናዎችን አሰባስቧል::
- ከ7 የብርዕና የአገዳ (cereals) ዝርያዎች የተሰበሰቡ የ32762 ናሙናዎችን፣ ከ8 የጥራጥሬ ዝርያዎች (pulses crops) የተሰበሰቡ የ4885 ናሙናዎችን፣ ከ6 የቅባት ዝርያዎች (oil crops) የተሰበሰቡ 2125 ናሙናዎች፣ በአጠቃላይ 40000 ለሚሆኑ ናሙናዎች ላይ የባህሪ ጥናት (morphological characterization) ተከናውኗል::
- በብዙ ናሙናዎች ላይ በሽታን የመቋቋም የባህርያት ትንተና አካሄዷል:: በጥቂት የአዝርዕት ዓይነቶች ላይ የተለያይነት (genetic diversity) ጥናትም ተካሄዷል::
- መጠናቸው ያነሰና የብቅለት አቅማቸው ከተወሰነው የብቅለት ደረጃ 85% በታች የሆኑትን በመስክና በላት ሀውስ በመዝራት፣ በማባዛትና በማደስ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቷል:: ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ ከ5000 በላይ የአዝርዕት ናሙናዎች ታድሰዋል፣ ከ7000 የአዝርዕት ናሙናዎች በላይ ተባዝተዋል::
- በአገሪቱ ውስጥ 12 የማህበራዊ ዘር ባንኮችን (community gene bank) በሦስት ክልሎች (በአማራ አራት፣ በኦሮሚያ አራት፣ በትግራይ ሁለት እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ ሁለት) በማቋቋም የገበሬ ዝርያዎች እንዲጠበቁና ለዘላቂ ጥቅም እንዲውሉ ተደርጓል::

### 5.2 የሆርቲካልቸር ጀኔቲክ ሀብት



- 4500 የሚጠጉ የቡና፣ 301 የሥራ ሥር እና 71 የቅመማ ቅመም ናሙናዎችን በጂማ ዞን በጮጬ መስክ ጅን ባንክ እንዲሁም 738 የሐረር ቡና ናሙናዎች በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በበዴሳ መስክ ጅን ባንክ እየተጠበቁ ይገኛል፣
- በአራተኛው ዙር የቡና ማሻሻያ ፕሮጀክት (CIP IV) በኦሮሚያና በደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል ለተቋቋሙት ሦስት የጫካ ቡና ዘቦታ ጥበቃ ቦታዎች /*in situ* conservation sites/ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን እንዲቻል ቴክኒካል ማንዋል በማዘጋጀት ተልኳል፣

### 5.3 የመድኃኒት ዕፀዋት ጀኔቲክ ሀብት



- ከ250 የመድኃኒት ዕፀዋት ናሙናዎች በላይ በዘር ጅን ባንክ ውስጥ፣ 320 ናሙናዎች በወንዶ ገነት መስክ ጅንባንክና 316 ናሙናዎች በባሌ መስክ ጅን ባንክ እየተጠበቁ ይገኛሉ።
- ከዓለም ባንክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ስለመድሐኒት ዕፀዋት አጠቃቀምና አጠባበቅ በተመለከተ የአሕዝቦት ሥራ የተካሄደ ሲሆን ይህንንም ለማጠናከር በኢትዮጵያ

ቴሌቪዥን፣ በራዲዮ ፋይናና በጉባ ትምህርት ማሠራጫ ራዲዮ በመጠቀም ሰፊ የማስተማሪያና የማስገንዘቢያ ትምህርቶች ተሠራጭተዋል፡፡

### 5.4 የመኖና ግጦሽ ዕፀዋት ጀነቲክ ሀብት

- *103 ናሙናዎች ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተሰብስበው በመስክ ጅንባንክ በመጠበቅ ላይ ናቸው፡፡*
- *315 የሄርባርየም ናሙናዎች ተሰብስበው ለተለያይነት ማመሳከሪያ ዝርያዎችን ለመለየት ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ይገኛሉ፡፡*
- *584 ናሙናዎች ከአንድ ተቋም በማስመጣትና የመለያ ቁጥር በመስጠት በጅን ባንኩ እንዲጠበቁ ተደርጓል፡፡*

### 5.5 የደንና ውኃ ውስጥ ዕፀዋት ጀኔቲክ ሀብት




- በ36 ደኖች ላይ ከተደረገው ኢንቬንተሪና ሶሺዮኢኮኖሚ ጥናት በተጨማሪ በ5 የቆላማ አካባቢ ደኖች ላይ የብዝሀ ሕይወት ኢንቨንተሪ (ምዝገባ)ና የአካባቢዎቹ የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት ጥናት ተጠናቅቆ መረጃው ለተጠቃሚዎች ተመቻችቷል፡፡
- በሀገሪቱ ደረቃማ ተራሮች ደኖች ውስጥ የሚገኙ የቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የዛፍ ዓይነቴዎች በጥናት ለመለየት መረጃዎች በመሰባሰብ ላይ ናቸው፡፡
- በ36 ትኩረት የተሰጣቸው የደን አካባቢዎች 1000 የተለያዩ የዛፍና የቁጥቋጦ ዓይነቴዎች የተመዘገቡ ሲሆን ለ405ቱ የዛፍ ዓይነቴዎች ላይ በቂ መረጃ ተጠናቅሯል፡፡
- የሀገሪቱ የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤና ምርምር ስልት ተነድፏል፡፡
- በከፍተኛ ደረጃ ለተመናመኑ የዛፍ ዓይነቴዎች (ለምሳሌ ኮሶ፣ዝግባ፣ዋርካና ቀረሮ) በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በ6 የዘቦታ እንክብካቤ ሥፍራዎች እየተጠበቁ ናቸው፡፡

- ስድስት የኢዘቦታ እንክብካቤ ሥፍራዎች ተቋቁመው ቅድሚያ የሚሰጣቸው 20 የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች፣ 50 ናሙናዎች፣ 33250 ችግኞች ፀድቀው በመጠበቅ ላይ ናቸው::

## 5.6 የእንስሳት ጀነቲክ ሀብት



- የሀገሪቷን የእንስሳት ሀብት ተለያይነት፣ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅና የወደፊት የአጠባበቅና ዘለቄታዊ አጠቃቀም አቅጣጭዎችን ለመቀየስ የሚያስችሉ ሥራዎች ተሰርተዋል::
- የሀገራችን የለማዳ እንስሳት የሚገኝበትን ሁኔታና የወደፊቱን የጥበቃና የዘለቄታዊ አጠቃቀም የትኩረት አቅጣጫ የሚያመለክት አንድ ሀገራዊ ሪፖርት በማዘጋጀት የዓለም አቀፉ (FAO SoW Report) ሪፖርት አካል እንዲሆን ተደርጓል::
- በተለያዩ መድረኮች እንዲሁም በፖስተሮችና በራሪ ጽሁፎች በመጠቀም በእንስሳት ጄኔቲክ ሀብት ጠቀሜታና አጠባበቅ ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል::

## 5.7 የደቂቅ ዘአካላት ጀነቲክ ሀብት



- ***በኦሮሚያና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልሎች በሚገኙ 20 ወረዳዎች ላይ ከደቂቅ ዘአካላት ጀነቲክ ሀብት ጋር ተያይዥነት ያላቸው የማህበረሰብ ልምዶችና ዕውቀቶች ተጠንተው መረጃው ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡***
- ***ከመስክ 684 የደቂቅ ዘአካላት ናሙናዎች፣ ከተለያዩ ተቋማትና ተመራማሪዎች 330 የሚሆኑ የደቂቅ ዘአካላት ናሙናዎች ተሰብስበው እየተጠበቁ ይገኛሉ፡፡***
- ***በተፈጥሯዊ አቀማመጡና ይዘቱ የተለዩ ዓለም አቀፍ ትኩረት ካለው የደናክል (አፋር) ስምጥ ሸለቆ በተለይም ከዳሎል፣ ደባሁ፣ አፍዴራና ኤርታሌ ከተሰበሰቡ 34 የደቂቅ ዘአካላት ናሙናዎች ዲ.ኤን.ኤ በመውሰድ በተካሄደው የላብራቶሪ ጥናት ከአራት የዲ.ኤን.ኤ ናሙናዎች 85 የባክቴርያ ዝርያዎችን ለመለየት ተችሏል፡፡***
- ***በደናክል ስምጥ ሸለቆ የተካሄደው የደቂቅ ዘአካላት ናሙና መሰብሰብና የላብራቶሪ ውጤት ቢ.ቢ.ሲ. በቀረፀው*** “The Hottest Places on Earth” ***በተሰኘው ፊልም ተካቶ በቢ.ቢ.ሲ. ዓለም አቀፍ ፕሮግራም አማካይነት ለዓለም ህብረተሰብ እይታ በቅቷል፡፡***

## 5.8 የኸርባርየምና የማቀዝቀዣ አገልግሎት



- ***53445 ናሙናዎች በረጅም ጊዜ ክምችት*** (-10$^{0}$C)፣ ***7140 ናሙናዎች በአጭር ጊዜ ክምችት*** (4$^{0}$C) ***እየተጠበቁ ይገኛሉ፡፡***
- ***76000 ናሙናዎች ለምርምርና ልማት አገልግሎት እንዲውሉ ለተለያዩ የምርምር እና ልማት ተቋማት ተሠራጭተዋል፡፡***
- ***ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ 22 የሀገር ውስጥ ቡድኖች እና 9 የውጭ አገር ቡድኖች በአገልግሎቱ ውስጥ የሚገኘውን ጅን ባንክ ጐብኝተዋል፡፡***
- ***ለ6 አገሮች*** (Burundi, Rwanda, Madagascar, Sudan, Yeman, Somalia) ***ተወካዬች በብዝሀ ሕይወት አጠባበቅ ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡***

## 5.9 የጥበበ ሕይወትና ደህንነተ ሕይወት

- የምግብ ንጥረ ነገር (አልሚ ምግብ፣ ቅባት፣ ቃጫነት፣ ማዕድናት እና አርጥበት) ይዘት መጠን ትንተና በ12 እህል ዝርያዎች በተገኙ 2984 ናሙናዎች ላይ ተካሄዷል፡፡
- በእንሰት፣ አንጮቴ፣ ኦሮሞ ድንች፣ በጤፍ ያልተላመዱ ዝርዎችና ---- ላይ የሳይቶሎጂ (ሥነ ህዋስ) ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡
- በእጽዋት (አዝርዕት) ላይ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመለየትና ለመከላከል እንዲቻል በላብራቶሪና በመስክ 4650 በሚሆኑ ናሞናዎች ማለትም በስንዴ፣ በገብስ፣ በማሽላ፣ በጤፍና በበቆሎ ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡

## 5.10 ኢትኖባዮሎጂ



- ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ውስጥ በኦሮሚያ በ11 ወረዳዎች፣ በአማራ በ4 ወረዳዎች በሰብል ነባር ዝርያዎች እና በደቡብ 3 ወረዳዎች፣ ከአፋር አንድ ወረዳ ውስጥ ዱር በቀል በሆኑ ዕፀዋቶች ዝርያዎች ላይ ያለውን ነባር ዕውቀት፣ ፈጠራና ልምድ በመሰብሰበና በመመዝገብ በ9 ወረዳዎች ላይ ያለውን መረጃ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች አመቻችቷል፡፡
- አንድ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና ፕሮግራም በኢንሳሮ ዋዩ እና በአንኮበር ወረዳዎች ላይ በማዘጋጀትና በማስተባበር ለሁለት ቀን 121 ለሚሆኑ ገበሬዎች ሥልጠና ሰጥቷል፡፡
- አንድ ዓለም አቀፍ የኢትኖባዮሎጂ ኮንፈረንስ በማዘጋጀት የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

**6. ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት**

- **በሀገራችን በሚገኙ የምርምር ማእከላት ከተለቀቁ 146 የተሻሻሉ ዝርያዎች መካከል 103 ያህሉ በጅን ባንኩ ከተከማቹት ነባር ዝርያዎች የተወሰዱ ሲሆኑ ይህም ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል፣**
- **በጤፍና ቬርኖንያ ዝርያዎች ሀገራችን ያላትን የጄኔቲክ ሀብት ባለቤትነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር ከሁለት የውጭ ኩባንያዎች ጋር የጥቅም መጋራት ሥምምነቶች ተፈርመዋል፣**
- **ሀገራችን የብዝሀ ሕይወት ዓለም አቀፍ ሥምምነት ፈራሚ በመሆኗ መ/ቤታችን የጽ/ቤቱ ተጠሪ በመሆን 5 ብዝሀ ሕይወትን የሚመለከቱ ብሄራዊ ሪፖርቶች ማለትም ለምግብነት የሚውሉ እጽዋት (2)፣ እንስሳት(1)ና አጠቃላይ ብዝሀ ሕይወትን በተመለከተ (2) ሀገሪቱ ተጠሪ ለሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ቀርበዋል፣ ስምምነቱን በሚመለከቱ ሥራዎችም ኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡**